# የመጨረሻው ሰይጣን
# ክፍል ሶስት
# ካለፈው የቀጠለ

- እንደምን ከረሙ እናቴ? ደህና ከርሙ ።
- ደህና ነኝ ።ምን እሆናለሁ ብለህ ።
- ማንበብ ጀመሩ ኑዛዜውን።
- አነበብኩት እንጂ ልጄ!! አነበብኩት ። አየኸው ያለውን ።

„በአለም ላይ ታላላቆቹ ጨካኞች እንኳን ሳይቀሩ አንድ ቀን ህፃን እነደነበሩና የእናት ፍቅር እንደሚያስፈልጋቸው ልትረዱት ይገባል ።“ ነው እኮ የሚለን ።

„የልጅ ፍቅር ፤ የእናት ፍቅር ፡ የአገር ፍቅር ፡ ሁሉም እኮ አንድ ነው ። መቼ ይለያያል ብለህ ። ከአለእናት ማደጉን አየሁት፡አነበብኩት።

„ልጄ የእናት ጡት እኮ ነው ሰውን ከአውሬነት ወደ ሰውነት የሚለወጥ ይባላል“። እናትኮ ነች ለሁሉም መድሃኒት“።

ምን ያድርገው
ቢያጣ እናቱን ፤
ቢሻ ፍቅሯን ፤
ቢናፍቅ ሽታዋን ፤
አንድ እናቱን ፤
ቢያልም የማያውቃትን ፤
ፍቅሩዋን ፤ ሳትሰጠው
ጥላው ሄደች እየወደደችው ።

እሱስ አላየኸውም እንዴ ፤ በስተመጨረሻው እኮ!!እናት ፍቅር ነች አለ፡ጨካኝም ህፃን ነበር ይበል ።ከአለ እናት ማደጉን ልቡ ውስጥ ከርሞ። አንተስ ትርሳው ይሆን ብዬ አላስብም። ያኔ በዛ በዶፍ ዝናብ ጥቁር ባለ ቀን ፤

እጅህንን በእግር ብረት ጠፍረው ሲወስዱህ
እናትህ የሆኑትን እስክትፈታ ታስረህ።
አንድ ጋቢ ላይ፤ደረቁ መሬት ላይ፡የተኙትን
ጠዋት ማታ ተንበርክከው የፀለዩትን
ጌታዬ የልጄን እሬሳ አታሳሰየኝ ያሉትን
በማለዳ እሬሳ የዳበሱትን የፈለጉትን።

እንዴት ልጄ ከባድ መሰለህ
ልብህ ሆድህ ውስጥ ሲንቦጫቦጭብህ
ያ ከመሀፀንህ የወጣው ልጅህ
መንገድ ወድቆ በደም ተጨማልቆ መግኘት መቻልህን ማወቅህ ።

ምን እናትህ ብቻ ፤ ሁላችንም እንጂ ፡ አለቀስን ጮህን

እሪ አልን አለቀስን፣ ተላቀስን
ተውት ጥሩ ልጅ ነው አልን
ጠመንጃ አውጥተው አስፈራሩን
እያለቀስን ለእግዜር ሰጥተን ተውን
ህዝብ ነን ምን አቅም አለን
ጠመንጃ የያዘ ሁሉ ሲያስገድደን
ማን ሰምቶን
ቢስሙንማ ቢጠይቁን
እንነግራቸው ነበር የምናምነውን።

ሳይጠይቁን ሲገርፉን ሲገድሉን ከርመው
ለሌላ ሰጥተው ጥለውን ጠፍተው
ቢመጣ ደግሞ ሌላው
የሚብስ ሆነ ከዛኛው ።

ስም ቢያጠፉ በውጭ ተቀምጠው
ማን ሊሰማቸው ተወው ።

አየኸው ልጄ እሱ እንኳ አውቆት ፃፈው
„የሰው ችግርን በሩቅ የማወቅ፤የመዳሰስ፤ችሎታ አለው“።
ይህንን እኮ ነው ኢአባነት የምልህ
ቅድም ጀምሮ የምነግርህ።

መሬት ላራሹ ስትሉ
ለጭቁኑ ስትሉ
አትግድሉ ስትሉ
ስልጣን ለህዝብ ስትሉ
ዴሞክራሲ አለገደብ ስትሉ
የስውን ችግር በሩቁ መዳሰሳችሁ፡ማወቃችሁ
እኮ ነው በህዝብ ያሰወደዳችሁ
በህብረተስቡ ውስጥ መንፍስ ያረጋችሁ።

እሂ በየቦታው አስር የሚፅፈውን ተወው
ሆድ ጭራቅ ነው ብሎ የተነሳ ትጉህ አሳማ ነው
ከሆዱ በላይ የለም የሚያሰበው
እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል አለች አሉ የቺ ፍጠር ነው ቋንቋው
የዛች የምስኪን ቋንቋ ይዘው
እሷ እንደሁ ጥራ ግራ ነው የምትኖረው
ለራሳችው ጥቅም ሲሉ ንግግሯን ለውጠው
ጥሩውን አስተሳስቦን  ስድበው
በእርሷ ስም የራሳቸውን አስተሳስብ ተናግረው።

በእርሷ ላይ እንዲህ ያሶሩ
በእናንተ ላይ ብዙ ቢያወሩ
ቢፅፉ ምን ቢደንቀን ቢቀባጥሩ።

እኮ እሱም ብሎ  መከራቸው

ትንኝ እንኳ አልግድልኩም!!!! ብላችሁ አትመፃደቁ አላቸው
ንስሃ ግቡ ምክንያት አትፈልጉ ብሎ ወቀሳቸው
ያውቃቸው የለ ከአመሰራረታቸው
ሌላ ምስክር ከየት እናምጣላችው ፡፡

የሰውን ችግር በሩቅ መረዳት ታላቅ ተስጥኦ ነው
የተፈጥሮ የውስጥ ምልክት ነው
አብሮህ የሚወለድ ነው
ደግነት ባህሪ ነው
ጨዋነት ጠባይ ነው
ሆዳምነት፤ ስግብግብነት፡ ሰይጣነዊ ምልክት ነው ።

ዛሬ ተነስተህ እንዲህ ነኝ ሰላልክም አይሆንም ። የትነበርክ ፤ስለኛ ምን ብለሃል መባልህ አይቀርም ። መውቀስ ቀላል እንደሚሆን መወቀስ ደሞ መራራ ነው ልጄ ። ቀን ተለውጦ አንተ የት ነበረክ ፤ምንስ አልክ ፤ ምንስ አደረግህ ስትባል ፤ መልስ ከሌለህ ሆድ አምለኩ ተብልህ ነው የምትታለፈው ።የሌሎች አለመኖር መደረግ ያንተን መኖር ከአጎላው ፤ የሌሎቹ መኖር የአንተን መክሰም እንደሚያመጣው እንዳታጣው ልጄ ። ስለዚህ ነው ልጄ የሰው ችግር የሚገባህ ሁን ብዬ ነው የምመርቀህ ። የጅብ ቋንቋ አይንኑረህ ነው የምልህ። የሆነ ሆነና የሰውን ትፅፋለህ ያንተስ መቼ ነው የሚፃፍ ?

- ይፃፈል እንጂ ይፃፋል ፡
  ካልተፃፈማ ማን ያውቀዋል። እናቴ።

- ይረሳል ልጄ ይረሳል ፡፡
  እቆየማ ይጠፋል።
  ለመሆኑ ምን ልትለው አስበሃል ።

- “እንደው በአፈሩ ላይ“

- ምነው ልጄ ካላጣኸው ስም ። የሙሾ ስም ።

- አዘን እናቴ ።

የጓደኞቹ ሞት
የተደራረበ ጉዳት
የተደራረበ ጭቆና፡ ሙሾ አውራጅ አደረገኝ ።
ለሞቱት ፤ ለጠፉት
ለተቀበሩት ፤ ላልተቀበሩት
ለሁሉም ፤ አለቅሳለሁ
ቢታወሱ ብዬ ሙሾ አውራጅ ሆንኩ
ላለፈውም አለቅሳለሁ
ለአሁኑም አለቅሳለሁ
ለወደፊቱም አለቅሳለሁ
ለጠፉት ዘመዶቼ
የት እንዳሉ ለማለውቀው ጓዶቼ

እንደው በአፈሩ ላይ ስል እከርማለሁ ።

- እኔስ ብሆን አዘን መች አጣሁ ብለህ ።
  የቀይ ሽብሩን ስል የኤርትራው
  የኤርትራውን ስተው የሶማሌው
  አንዱን ስጨርስ ሌላው ።
  የትልቁን ስረሳ የትንሹን
  የትንሹን ስረሳ  የትልቁን
  የማሙሽንስ ይሁን ያስመሮምን
  ከዛም ደግሞ የባድመውን
  የኤድሱም ይሁን  የሌላውን
  ከዛም በሆላ የወያኔውን።

የጓደኛህን ጠይቀህ  ምነው
የታላቁን ልጄን እረሳሽው።
አልሰማሽውም እንዴ
እኔው እራሴ በደም ወኝቶ እንደገኘሁት
እቤቴ በረፍ ላይ አስተኝተውት።
ልጄን ቆሻሻ መስሎኝ  ላልፍ ረግጨው
አምጥተው እዚያ ይጥሉታል  ብዬ መች አስቤው።
የተከመረ ነገር መስሎኝ እንጂ መች አውቄው።
እንዳገኘው ብለው ነው እንጂ ልጄን እራሴው
ልጄን የመጀመሪያውን ከመሀፀኔ የተወለደውን።
ያውቂታል ጠዋት እንደምሄድ ቤቴክርስትያን ።

ምን አይነት ጭካኔ ነው፤ ምን አይነት ጭካኔ ነው፤ምን አይነት ጭካኔ ነው።

- አስታውሻወለሁ እንጂ እናቴ ። እንዴት እረሳዋለሁ አሰተማርዬን ። ፊደል አስቆጣርዬን ። የቆየ ሀዘን እንዳልቀሰቅስ ብዬ እንጂ ።

- የቆየ ሀዘን አልክ። የልጅ ሞት እኳ አያረጅም ልጄ ። ጠዋት ማታ ይረሳል ብለህ ነው ። ከተረሳማ ሰውነታችን ምኑ ላይ ነው ።የጓዶችህን ሞት ትረሳዋለህ።

- እንሱማ አውቅዋለሁ እናቴ ። እሱን ብዬ አደል ሙሾ አውርጅ የሆንኩ ። የወንድ ሙሾ አውራጅ ብዙ የለም ። ሆንኩ እንጂቢብስብኝ ። ለወጉማ ታላቁ ኢትዮጵያዊ ሎርት ፀጋዬ ወንድ ልጅ ተደብቆ ነው  የሚለሰቅሰው ብሎ አልነበር። ። አልወጣልህ ቢለኝ ሙሾ አውርጅ ሆንኩ ።

- እንግዲህ አትፍራ አብረን እናለቅሳለን ።

ውይ ውይ ውይ
ሊሞሉበት ነው አፈር ሊሞሉበት ነው መረሬ
በዐይኑ ከለላ በዐይኑ ዳር ዳር።

እኩለ ሌሊት ላይ ከቤትሽ አጠገብ የሎኽው ጥይት
ነድሎልሽ አረፈው የልጅሽን ደረት።
ነጋ አለነጋ ብለሽ ሌሊት በዳበሳ
አግኝተሽ አረፍሽው የልጅሽን ሬሳ።

ምን ብሎ ይሆን ሆድሽ
ምን አለ አንጀትሽ
ለዕድሜ ልክ የሚሆን እዬዬ ሲሰጥሽ።

- ተወኝ ልጄ ፣ ተወኝ ፡ተወኝ ። ቢገኝ ኑሮ አፈር ቢለበስ እንዴት ጥሩ ነበር ። ከለከሉኝ እሬሳውን እንዳልነካ ። ጮሁኩኝ አለቀስኩ ። ተሰበሰብን እሪ አልን ።

    ደረት ተመታ ።
    ትንሽ አለፍ ብሎ እትብቱ ከተቀበረበት ቦታ።

  ውይ ውይ ውይ
  እንደው ባፈሩ ለይ በተደመደመው።

አልበላም አልጠጣም ጠሙን ነው የከረመው
የመንግስቱ ካድሬ ራርቶለት ይሆን ጥይት ያጎረሰው።

ሊሞሉበት ነው አፈር ሊሞሉበት ነው መረሬ
በአይኑ ከለላ በዓይኑ ዳር ዳር ።

የደራ ነበረ የዛሬ ገበያ ሸማቹ የበዛ
የጥይቱን ክፍሎ ሬሳ ሲገዛ
ጮኬ እንዳላለቅስ ሬሳ ልቀማ
ተስማምቼ መጣሁ አንጀቴ እየደማ።

  አልቻልንም ጮህን ። ነጠቁን አሰከሬኑን ። አበድን ። አበድን።የት እንደጣሉት ሳናውቀው ቀረን።

- ይልቅ ስለዚያ ጨካኝ ይሻለኛል ።

- ምን ገዶኝ ።

የመጨረሻው ሰይጣን ካለፈው የቀጠለ ።

እያደግሁ ስመጣ ክፋቴ እየበዛ መጣ። ልጆች ማደባደብ በሱም መሳቅ በጣም የምወደው ስራዬ ነበር።አባቴ በሰፈራችን በጣም የተፈራ ነበር ። የሰፈሩ ሰው በጣም ይፈራዋል ። ለምን አባቴን ሰዎች እንደሚፈሩት በሁዋላ ነው እያወቅሁ የመጣሁት። ሁለም ሰው ክፉም ልስራ ደግም፡ የዛ የርኩስ ልጅ ነው ያደረገው ነው የሚባለው።

አባቴ በወጣትነቱ እንደኔ እንደነበረ ማወቅ አላዳገተኝም ። ከሰው ተጣልቼ እያለቀሰኩ ከመጣሁ መልሶ እኔኑ ይገርፈኛል።

  ድንጋይ መቶ ብር ያወጣል?
  ምን ሆነህ ነው ተሸንፈህ የምትመጣ?
  ብሎ ገና መመታቴን ሲያስበው ሲቃ ያንቀዋል።

እኔም በሁዋላ እያለቀሰኩ ወደሱ መሄድ አቆምኩ። አንድ ቀን ከከአንድ ልጅ ጋር ተጣለሁና ልጁን ብመታው ። ልጁም እያለቀሰ አባትህ የሰው ስጋ በልቶአል አንተም የኔን ስጋ ልትበላ ነው እንዴ አለኝ። ሌሎቹ ልጆች በጣም ስለሳቁ ሄጄ አባቴን ብጠይቀው ማን እንዳለኝ አንዳሳየው ከጠየቀኝ በሆላ እልጁ ቤት ሄደን የልጁን አባት ጠርቶ ለምን ለልጁ ይህንን እንደነገረው ጠየቀው። ሰውየውም የሚመልሰው ቢያጣ ዝም ቢል አባቴ ሰውየውን አንዳይሞት እንዳይተረፍ ከደበደበው በሆላ ለፖሊስ እነዳይነግር አስጠንቅቆ ሄድን። ከዛ ቀን ጀምሮ አባቴን በጣም እፈራው ጀመርኩ።

አንድ ቀን እንጀራ እናቴ አንድ እንግዳ መጥቶ ሰውየውን ይዛ ለቅሶ ቤት እንደሄደች። ሰውዬውን በደንብ ሳልመለከት እቤት ገብቼ እሊጋውን ከበታተንኩ በሆላ አባቴ መምጫው ሰለነበር እደጅ አጠብቀው ጀመር ። ልክ ሲገባ እቃውን ማን እንደዚህ እንዳደረገ ጠየቀኝ። እኔም ምንም እንደማላወቅ ነገርከት። እናትህ የት አለች ቢለኝ እንደተለመደው መልስ አልሰጠሁትም ። እናትህ ሲባል እንደማልወድ የሚያውቀው አባቴ ስሚን ጠርቶ የት አለች አለኝ። እኔም ከአንድ ሰውዬ ጋር እዚህ ቆይተው አሁን እንደወጡ ነገርኩት። ወዲያውኑ አባቴ ደሙ ሲፈላ አየሁት። ባስቸኳይ እነድጠራት አድርጎ ገና እቤት ስትገባ በዱላ ተቀበላት። በጣም የደነገጠችው እንጀራ እናቴ አባቴ እግር ውስጥ ተደፍታ አርባ አራቱን ታቦት እየጠራች እንዲተዋት ትለመነው ገባች። አባቴ እልኩ ሲበርድለት ለመሆኑ ማነው የመጣው ብሎ እንጀራ እናቴን ጠየቃት ። እስዋም የመጣው ወንድሙ እንደሆነና ከአዲስ አበባ መጥቶ ለቅሶ ቤት እንደወሰደችው ነገረችው። ምን ሊሆን አልጋ ላይ እንደወጣ ቢጠይቃት ባለ በሌለ ታቦት ምላ እንደዚህ አይነት ነገር እንዳልነበረ ነገረችው። አባቴ ምንም ሳይናገር ፈገግታ አሳይቶ ምግብ ሰርታ እንደትጠብቅ ነግሮአት ወደ ለቅሶ ቤት ሄደ። ሁኔታው ለኔ ግራ ቢገባኝም አባቴን እውነቱን ነግሬ ይቀርታ እንድጠይቀው እንጀራ እናቴ ብትጠይቀኝ እኔ አሻፈረኝ አልኩ። እርሷም ውርድ ከራሴ ብላ ዝም አለች። አጎቴ ተመልሶ መጥቶ ሲበላ ሲጠጣ ተመሸ። ለመጀመሪያ ግዜ አባቴ ተደስቶ አየሁት። ወንድሙን በጣም ይወድ እንደነበር የተገነዘብኩት የዛን ቀን ነው።

በበነጋታው አጎቴ ወደ አዲስ አበባ ሲመለስ አኔን እዚህ ያለውን ትምህርት ሰትጨርስ አኔጋ ሆነህ ትምህርትህን ትጨርሳለህ ብሎኝ ሄደ። አባቴ እሱን ሸኝቶ እነደመጣ በቀጥታ ወደ ቤት ገባና እኔን ጠርቶ ሰለትላንትናው ጠየቀኝ። እኔ አሁንም ጭንቅላቴን ቀብሬ የማውቀው ነገር እንደሌለ ነገርኩት ። እሱም አይኑን እያየሁ እንደገና እንድነግረው ነገረኝ። ያን ማድረግ ስላቃተኝ አባቴ ወዲያውኑ እኔ እነዳደረግሁት ገባው ። ሁለት እጆቼን ይዞ ከመሬት ከጣለኝ በሆላ በበሬ ቆለጥ በተሰራ አለንጋ ይገርፈኝ ጀመር። እንባዬን ውጬ አይኔን አፍጥጬ በዕልክ መጓጓጥ ጀመርኩ። ግርፉ በረድ ሲል በቀሰተታ ከጓዳ ወሰጥ እንጀራ እናቴ ስታለቅስ ይሰማኝ ነበር።አባቴ እጅን እግሬን ጠፍሮ ካሰረ በሆላ ወደ ውጭ ወጥቶ ማር ሲቆረጥ ጭስ የሚጨስበት ገል ይዞ መጣ። እንጀራ እናቴንም እሳት አንደታመጣበት ገሉን ሰጣት።እሷ እሳቱን እስክታመጣ ድረስ እግሮቼ የታሰሩበተን ገመድ ጎትቶ ከምሶሶው ላይ አርጎ ቢጎትተኝ እግሬ ወደላይ ጭንቅላቴ ወደ ታች ተንጠለጠለ።እንጀራ እናቴ እሳቱን ስታመጣ አባቴ እንድትወጣ አዘዛት። ልመና ልትጀምር የዛሬን ስትል በጨኸት መድረሽ አሳጣት። እሷም እየተዋከበች ወጣች ። ሸማ አውርዶ አፍንጫውን ከሸፈነ በሆላ ገሉን አጭንቅላቴ ስር አድርጎ ከጓዳ የበርበሬውን ቅል ይዞ መጣ። በርበሬውን አውጥቶ እገሉ ላይ ያለው እሳት ላይ ቢያደርገው በአፍንጫዬና በአይኔ የገባው የተቃጠለ በርበሬ በሀይል ያቃጥለኝ ጀመር። ስቃዩ ስለበዛብኝ አባቴን እለመነው ነበር ። በመጨረሻ ከውጭ በጣም ተንኳኳና በሰፈራችን የነበሩ የታወቁ ሽማግሌ የጣሩ ጀመር ። አባቴም ዝም አለ ።

- ሽማግሌው አይሆንም በሩን ከፈት ልጁን ትገለዋለህ ።

- ይሙት ይህ እርጉም ተርፎስ ምን ሊጠቅም።
- እርሱ የእግዜር ጉዳይ ነው። ይጥቀም ይጉዳ አንተ አደለህም የምትወስነው።አሁን በሩን ክፈት በጊዮርጊስ ይገፔሃለሁ።

ምንም ሳይናገር የጊዮርጊስን ስም ሲሰማ በሩን በርግዶ ከፈተው ። በሩ ሲከፈት የበርበሬው ሽታ በጣም ሰለሰነፈጋቸው በከፍተኛ ካስነጠሱ በሁዋላ

- ሳእለን ቅደሰት ልትገለው ፈለግህ ወይ በሉ አሁን አውርዱት ብለው አብረዋቸው የመጡትን ልጆች አዘዙዋቸው። ለብዙ ቀናት ታምሜ ከረምኩ ። የዛ ግዜ ነው ጥርሴ የተሰበረው ።

በትምህርቴ ግን የረብሻዬን ያህል ጎበዝ ነበርኩ። ገና ቄስ ትምህርት ቤት ሆኜ ኤኔታ ወልዴ የሚባሉ አሰተማሪ ሁል ጊዜ አይ ጉብዝና ተንኮል ባይጨመርበት እያሉ ይናገሩ ነበር ። ጢማቸው ረጅም በመሆኑ እወዳቸው ነበር። እሳቸው ላይ እንኳ እንቅልፍ ሲወስዳው እያሾፍኩ ልጆቹን አስቅባቸዋለሁ። አንድ ቀን ከየቤቱ የተሰበሰበላቸው ጠላ ወስጥ ውሃ ጨምሬ በጣም ተናደዱ። ማን እንደሆን ቢጠይቁ ሁሉም ልጆች ወደኔ ማየት ጀመሩ ።እሳቸውም ማን እንዳደረገ እኔን ሲጠይቁኝ አንድ ልጅ ላይ አሳበብኩበት። እሳቸውም እውን ነው ብለው ቢጠይቁት ልጁ አለቀሰ ። እሳቸውም እርሱ ያደረገ መስሎአቸው ልጁን ቆነጠጡት፡፡ ትምህርት ሲያልቅ ማለት የነበረብንን ማለት አልወድም ነበር።

በኤነታ ጉሮሮ ጠጅ ይንቆርቆር
በኔ ጉሮሮ አጥንት ይቀርቀር።
ማለት ቃሉ እራሱ ጉሮሮዬን ያንቀኝ ነበር።

እናቴ እኔን ሰለማትወደኝ የሞተች ነበር የሚመስለኝ ። ግን ስለሷ ብዙ ማወቅ ብፈልግም አባቴን ጠይቄው አላቅም። ስለስዋ የማቀው እሱ የነገረኝንና የሰፈሩ ሰው የሚያወራውን ብቻ ነው። አባቴ አንዳንድ ግዜ ስለስዋ ሲያነሳ እንባ እያቀረረው ። በጣም ቆንጆ ነበረች። ከማንንም የትበልጥ። ምኗም ምንዋም ከነዚህ እርኩሶች የተሰወለደች አትመሰልም፡፡ የእናቴ ዘመዶች አንዳንዴ መንገድ ላይ ሲያገኙኝ። „የዚያ የረኩስ ልጅ ምን አከለ እባካችሁ“ ይሉኝ ነበር። እነርሱም አይቀርቡኝ እኔም ደግም እንደዘመዶቼ አላሰባቸውም ነበር።

እያደግሁ በሄድኩበት ጊዜ አባቴ ስላለፈው ጊዜ ይነግረኝ ጀመር።እናትህ በእምዬ ማርያም ምስል የተሰራች ነበረች። አባትዋም ባለፀጋ ሆኖ ሳለ ሰው ማክበር ያዳግተው ነበር። ይህ መሬት ፤ይህ ቤት፤የኛ ፤ነበር።እነዚህ እርጉሞች ካሳ በሉት እንጂ ይለኛል።መጀመሪያ አይገባኝም ነበር ። በሁዋላ ግን ሁሉም ነገረ ገባኝ።

አባቴ እናቴን እንዳዬ በፍቅር ይነደፋል። ውሃ የምትቀዳበት እየሄድ ማሸከርመም ይጀምራል። እናቴም ወንዳ ወንድ ጠባዩን ሻካራ እጆቹን መውደድ ትጀምራለች። ውሃ እንኳ እቤት ቢኖር ደፊታ ትጨርሳለች። አባቴም ያለውን ስራውን ጨርሶ እሷን ለማገኘት ሁል ጊዜ ይጣደፋል። ወሬ አይደበቅም እና ይህ ነገር አባትዋ ጋር ይደርሳል። አባቱዋም ይህ የደሃ ልጅ ልጄን ሳያበላሻት ብለው ለሌላ ሀብታም በዕድሜ የማይጥማት በቅርብ ሚስቱ የሞተችበት ለመዳር ማሰባቸው የሰማል። አባቴም እኔ ሳልሞት ማንም እሷን አያገባም ማለት ይጀመራል። ይህን ጊዜ አባቴ ጠመንጃውን በቅርብ ደብቆ ወደ እናቴን ሊያገባ የነበረው ሰው ጋ ሄዶ እናቴን እንደሚወዳት ይነግረዋል። ሰውየውም አባቴ ባዶ እጁን መሆኑን አውቆ አባቴን አዋርዶ ሰድቦ ያባርረዋል፡፡አባቴም ጠመንጃው

ከደበቀበት አመጥቶ ሁለት ጥይት ተኩሶ ሰውዬውን ገድሎ ወደ እናቴ አባት ቤትም ሄዶ አያቴን፤ የእናቴን አባት ገድሎ  ያመልጣል። ከዛም ጫካ ገብቶ ይሸፍታል።

ጫካ በነበርት ጊዜ በጣም ግፍ እንደሰራ ይነገርለታል። ሰዎችን መንገድ ላይ እየጠበቀ ምግብ ወይም የሚፈልገውን እንዲያመጡለት ያስገድዳቸው ነበር። አንድ ጊዜ አንድ ሰው ለፖሊስ ነግሮ ተደብቀው ይጠብቁታል። አባቴ በድንገት ጫካው ውስጥ አዲስ ኮቴ ስለተመለከተ በጣም ስለተጠራጠረ ቀስ ብሎ ወደ ቦታው ይሄዳል። በቦታው ሰዎች ተደብቀው ያገኛል። ቀስ ብሎ ተሸሽጎ ወደ አጋለጠው ሰውዬ ቤት ሄዶ ጎጆውን በውጭ ዘግቶ ሰውየውን ከነልጆቹ ከነህይወታቸው አቃጠላቸው ። እሳቱን ለማጥፋት ከጎረቤት የመጡትን ሰዎች በጥይት ያባርራቸዋል። ሰውየው ከነልጆቹ በተዘጋ ጎጆ ውስጥ በሳት ተለብልቦ ይሞታል። ትኩሱ ስጋ በሳት ተጠብሶ ሽታው ለብዙ ጊዜ አልጠፋም ነበር ይባላል። አባቴ ግን ልጆቹ በእሳት በሚቃጠሉበት ጊዜ በደሰታ ይስቅ እነደነበር ይነገራል።  ከዛ በሆዋላ አባቴ በየመንገዱ እየዘረፈ ሴቶችን እየደፈረ ይኖር ጀመር።

ይቀጥላል ።